# ሙሉ/ፍጹም ሰው ወደመሆን ማደግ ኤፌ 4:12-13

1ተሰ 5:23
የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።

1. ስሜታዊና አካላዊ ህዋሶቻችንን በሥራ ማስለመድ
2. ፈቃዳችንን በተገለጠ ፈቃዱ ለመምራት
3. ….

## ክፍል 1 : የሰው ፈቃድ / ምርጫ

ሉቃ 22:39-42
ወጥቶም እንደ ልማዱ ወደ ደብረ ዘይት ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ደግሞ ተከተሉት። ወደ ስፍራውም ደርሶ። ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ አላቸው። ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም። አባት ሆይ፥ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።…

47-53: ገናም ሲናገር እነሆ፥ ሰዎች መጡ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱም ይሁዳ የሚባለው ይቀድማቸው ነበር፥ ሊስመውም ወደ ኢየሱስ ቀረበ።ኢየሱስ ግን፦ ይሁዳ ሆይ፥ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን? አለው። በዙሪያውም የነበሩት የሚሆነውን ባዩ ጊዜ። ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን? አሉት። ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው። ኢየሱስ ግን መልሶ፦ ይህንስ ፍቀዱ አለ፤ ጆሮውንም ዳስሶ ፈወሰው። ኢየሱስም ወደ እርሱ ለመጡበት ለካህናት አለቆችና ለመቅደስ አዛዦች ለሽማግሌዎችም። ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጎመድ ይዛችሁ ወጣችሁን? በመቅደስ ዕለት ዕለት ከእናንተ ጋር ስሆን እጆቻችሁን አልዘረጋችሁብኝም፤ ይህ ግን ጊዜያችሁና የጨለማው ሥልጣን ነው አላቸው።

2ሳሙ 24:1,10
1፤ ደግሞም የእግዚአብሔር ቍጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፥ ዳዊትንም። ሂድ፥ እስራኤልንና ይሁዳን ቍጠር ብሎ በላያቸው አስነሣው።
10፤ ሕዝቡንም ከቈጠረ በኋላ ዳዊትን ልቡ መታው፤ ዳዊትም እግዚአብሔርን። ባደረግሁት ነገር እጅግ በድያለሁ፤ አሁን ግን፥ አቤቱ፥ ታላቅ ስንፍና አድርጌአለሁና የባሪያህን ኃጢአት ታርቅ ዘንድ እለምንሃለሁ አለው።

1ዜና 21:1
1፤ ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሣ፥ እስራኤልንም ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው።

መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ እንደማይጋጭና ከላይ የተጠቀሱት ክፍሎችና ሌሎችም ስለፈቃድ የተጻፉልን ሃሳቦች

**ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በቤ/ክ / በቅዱሳን መሃል/ ግራ መጋባት ያለባቸው ነገሮች**
- ለሰው ስለተሰጠው ፈቃድ ምንነትና የእ/ር ፈቃድ ከሰው ፈቃድ ጋር ያለውን ግንኙነት
- እንደሰውና እንደአማኞች የተሰጠንን ሃላፊነትና ተጠያቂነትን
- የምርጫዎቻችንንና ውሳኔዎቻችንን ሃይል በተመለከተ
- ፈቃዳችንን በአግባብ ያለማስተዳደርና የሌሎችን ፈቃድ የመጫንን አደገኛነት

**ግራ መጋባቱ በግልጽ ከሚይባቸው ነገሮች መሃከል ዋና ዋናዎቹ:**
ሀ) የግል ድነትና የወንጌል ሥርጭት
(እ/ር የሚድኑትንና የሚጠፉትን አስቀድሞ ከወሰነ…)
- በእርሱ የሚያምን ሁሉ.., ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ.., ወደሞት የሚነዱትን ታደግ

ለ) ጸሎት
(ሁሉ በእርሱ ፈቃድ የሚወሰን ከሆነ... )
- አትለምኑምና አትቀበሉም..., ወደፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ, አባታችን ሆይ.. የእለት እንጀራችንን ስጠን.., ስለኢየሩሳሌም የሚለምኑ ጉበኞችን አቁሜአለሁ, የነነዌ ንስሃ

ሐ) የእ/ር ጥበቃና ደህንነት
(ሁሉ ለበጎ ነው ስለተባለ…, መከራ መጽሃፍ ቅዱሳዊ ስለሆነ)

- ጥንቃቄ ይጠብቅሃል.., ቅጥርን የሚያፈርስ እባብ ትነድፈዋለች

መ) በምድር ለሚሆነው ነገር ሰዋዊና ክርስቲያናዊ ሃላፊነት

ነጻ ፈቃድ ያለው / Free Moral Agency: ዘፍ 2:16,17; 3:1-7; 1 ቆሮ 10:13; ዕብ 4:15; 11:25; ኢያሱ 24:15; 1 ነገ 18:21; መዝ 119:30; ዘዳ 30:15-19; ኢሳ 1:18-20; ማቴ 23:37; 13:14,15; ራዕ 3:20; 22:17

<u>ለምን አስፈለገ?</u>

ውን ከሌሎች ፍጥረት የሚለየውና ሰው የሚያደርገው ተፈጥሮአዊ ማንነቱ ስለሆነ

- የሰው ሁለንተና / መንፈስ ነፍስ ሥጋ / አእምሮ/ ኅሊና፣ ፈቃድ፣ እውቀት፤ ስሜት፣ ፍላጎት፤ እንዲሁም አካል (1ተሰ 5:23፤ ቆላ 3:10፤ ኤፌ 4:24፤ ማቴ 26:41)
- እ/ር ሰውን በደመነፍስ የሚመላለስ ፍጡር ወይንም እንደተንቀሳቃሽ ማሽን/ሮቦት የራሱ ባልሆነ ፈቃድ የሚንቀሳቀስ አድርጎ አልፈጠረውም!

2) ሰው በእ/ር መልክና ምሳሌ የተፈጠረ በመሆኑ በመምረጥና በመፍቀድ ችሎታው የፈጣሪውን ክብርና ሉዓላዊነት እንዲያሳይ ስለተፈለገ

- ሁሉ ሃጢያትን ሰርተዋል የእ/ርም ክብር ጎድሏቸዋል

<u>ቀድሞም አሁንም ፈቃድ ያለን መሆኑ</u>

ዘፍ 13:9፣ 14:23፣ 18:5፣ 21:24፤ ራዕ22:17፤ ማቴ16:24፤ሉቃ9:23-24፤ ዮሐ 1:13፤1ቆሮ 7:36-37

<u>መምረጥ የማንችለውና የምንችለው</u>

- የማንመርጣቸው ነገሮች:- ወደዚህ አለም መምጣትን፣ ወላጆቻችንን፣ የምንወለድበትን ሥፍራ፣ የአገልግሎት ሥጦታን
- ከምንመርጣቸው ነገሮች መሃል:- የዘላለም ሕይወትን፣ መቀደስን፣ እ/ርን ማገልገልን፣ ለእ/ር የምንሰጠውን፣ የትዳር ጓደኛን / አዳም፣ የምንሰራውን ሥራ/ የምንማረውን ትምህርት፣

ዘዳ 30:15-20

15፤ ተመልከት፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፥ ሞትንና ክፉትን አኑሬአለሁ።
16፤ በሕይወትም እንድትኖር እንድትባዛም፥ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት
ምድር እንዲባርክህ፥ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ
ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ። 17፤ <u>ልብህ ግን ቢስት
አንተም ባትሰማ፥ ብትታለልም</u>፥ ለሌሎችም አማልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም፥
18፤ ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ
በምትገባባት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም። 19፤ በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና
መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ
<u>አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤</u> 20፤ እግዚአብሔርም ለአባቶችህ
ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፥ እርሱ
ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን <u>እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም
ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ።</u>

ዜና ቀዳማዊ 29:5

በሠራተኞች እጅ ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ለወርቁ ዕቃ ወርቁን፥ ለብሩም ዕቃ ብሩን ሰጥቻለሁ። <u>ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስ ማነው?</u>

ዘጸ 35:21-2

ከእነርሱም ሰው ሁሉ <u>ልቡ እንዳነሣሣው መንፈሱም እሺ እንዳሰኘው</u> ለመገናኛው ድንኳን ሥራ ለማገልገያውም ሁሉ ለተቀደሰውም ልብስ ለእግዚአብሔር ስጦታ አመጡ። ወንዶችና ሴቶችም <u>ልባቸው እንደ ፈቀደ</u> ማርዳዎችን፥ ሎቲዎችንም፥ ቀለበቶችንም፥ ድሪዎችንም፥ የወርቅ ጌጦችንም ሁሉ አመጡ ሰዎችም ሁሉ የወርቅ ስጦታ ወደ እግዚአብሔር አቀረቡ።

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች ስለሰው ፈቃድ</u>

1) ሰው ለመዳኑ / ለአለመዳኑ ተጠያቂ ነው! / ማር16:15-16፣ ሉቃ 13:3፣5፣ ዮሐ 3:16
2) ሰው ሁሉ (ቢፈቅድ) ይድን ዘንድ የእ/ር በጎ ፈቃድ ነው /ዮሐ 3:16፣ 1ጢሞ 2:4፣ 2ጴጥ 3:9
3) ሰዎች እ/ርን እንዲመርጡ ታዘዋል / ኢያሱ 24:15፣ ሉቃ 13:3
4) ሰዎች እ/ርን ባይመርጡ በእርግማን ሊኖሩ ተወስኗል / ምሳ 1:29-33፣ ማር 16:16

5) እ/ርንና ሰይጣንን እኩል ደስ ማሰኘት አይቻልም / ማቴ 6:24፣
6) የእ/ር ተሰፋ ቃል የሰዎችን የመታዘዝ ፈቃድ ተመርኩዞ ተሰጥቷል / ማር 3:35፣ 16:16፣ ዮሐ 5:40
7) ከ4000 በላይ ስለ ፈቃድ በተጠቀሰባቸው ስፍራዎች አንድም ቦታ እ/ር የሰውን ፈቃድ በግድ ያስቀየረበት ወይንም እርሱን እንዲቀበሉት ያስገደደበት ስፍራ የለም፤ የሰውና የእ/ር ግንኙነት በፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው / ዮሐ 7:17፤ 1ጴጥ 5:2

================================

# ክፍል ሁለት - የሰው ፈቃድ እና የእ/ር ፈቃድ

የእ/ርን ፈቃድና የሰውን ፈቃድ ግንኙነትና አሠራር በተመለከተ በቤ/ክ ለብዙ ዘመናት ለዘለቀውና ዛሬም ላለው ውዥንብር መነሻ ከሆኑት ሃሳቦች ዋናዎቹ

1) የእ/ር ሉዓላዊነት (Sovereignity) ጉዳይና
2) አስቀድሞ የመወሰን (predistination) አስተምህሮ

1-"ሉዓላዊ ከሆነ ሁሉን ይቆጣጠራል ይወስናል"
እ/ር ሉዓላዊ ቢሆንም የማንንም ሰው ፈቃድ ጥሶ በግድ የሚያደርገው ነገር የለም
ራዕ 3:20 / እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።
1ኛ ጴጥ 5:1-3 / እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤

ነጻ ምርጫም ስለሆነ በመጨረሻ ሰው በሰማው በእ/ር ቃል ይጠየቃል
ዮሐ 12:48 / የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል።

2- "አስቀድሞ የወሰናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው.../ ሮሜ 8:30"
በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደተቀመጠው በአስቀድሞ መወሰን (predestination) ወይንም መመረጥ (election) የእ/ር አላማ/ ሃሳብ:

ፍቅር ነው! (ኤፌ 1:4-5; 1ኛ ዮሐ 4:7)
ጥበብ ነው! (ሮሜ 11:33; 16:27), እና
ፍጹም ነው! (ዘፍ 18:25; ሮሜ 3:4-6)
እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው በሥራውም ሁሉ ቸር ነው። / "The Lord is just in all his actions, and exhibits love in all he does" (መዝ 145:17)

እ/ር የሰውን ነጻነትና ሃላፊነት በሁሉን-አቀፍ ዘላለማዊ ፈቃዱ ውስጥ እንዴት አጣጥሞ እንደሚያካትተው ያውቅበታል። አንዱን በመካድ ማስታረቅ አይቻልም!

**የእ/ር ፈቃድ ደረጃዎች**

1) የእ/ር ዘላለማዊ/ ሉዓላዊ ፈቃድ:- በአብዛኛው ያልተገለጠ ሆኖም ልንረዳ በምንችለው ልክ ስለእኛ ያለውን በቃሉ ያመለከተን፤ ሰውንና ፍጥረታትን በዘላለም ሃሳቡ ለአላማው መፍጠሩ፤ ጊዜንና ሥፍራን መወሰኑ (
2) ለሰው ልጆች በሙሉ ያለው ፈቃድ:- በክርስቶስ የዘላለም ሕይወት፤ ወደ እውነት እውቀት መምጣት (1ጢሞ 2:4; ዮሐ 3:16)
3) ለቅዱሳን/ ለአማኞች ያለው ፈቃድ:- ፍጹም እ/ርን መምሰል፤ የሁለንተና መቀደስ፣ መልካም የሆነውን ሥራ ለመስራት (ኤፌ 4:4-11, 1ተሰ 5:23)

**የእ/ር ፈቃድ ዓይነቶች**

1) የእ/ር ፍጹም ፈቃድ (perfect Will) - ከልቡ ሃሳብ/ፍላጎት ጋር የሚሄደውና ደስታው ሆነው
2) የእ/ር የመፍቀድ/የይሁን/ ፈቃድ (permissive Will) - በተለይ ከሰው ልብ ክፋትና እልከኛነት የተነሳ እንዲሆን የሚፈቅደው

1ኛ ሳሙኤል 8:1-9
እንዲህም ሆነ ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ ልጆቹን በእስራኤል ላይ ፈራጆች አደረጋቸው። የበኵር ልጁም ስም ኢዮኤል፥ የሁለተኛውም ስም አብያ ነበረ። እነርሱም በቤርሳቤህ ይፈርዱ ነበር። ልጆቹም በመንገዱ አልሄዱም፥ ነገር ግን ረብ ለማግኘት ፈቀቅ አሉ፥ጉቦም እየተቀበሉ ፍርድን ያጣምሙ ነበር። የእስራኤልም ሽማግሌዎች ሁሉ ተሰብስበው ወደ ሳሙኤል ወደ አርማቴም መጡና። እነሆ፥ አንተ ሸምግለሃል፥ ልጆችህም በመንገድህ አይሄዱም አሁንም እንደ አሕዛብ ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ አድርግልን አሉት። የሚፈርድልንም ንጉሥ ስጠን ባሉት ጊዜ ነገሩ ሳሙኤልን አስከፋው ሳሙኤልም ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው። በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ። ከግብጽ ካወጣኋቸው ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን ትተው እንግዶች አማልክት በማምለካቸው እንደ ሠሩት ሥራ ሁሉ እንዲሁ በአንተ ደግሞ ያደርጉብሃል። አሁንም ቃላቸውን ስማ ነገር ግን ጽኑ ምስክር መስክርባቸው፥ በእነርሱም ላይ የሚነግሠውን የንጉሡን ወግ ንገራቸው።...

9:15-16 ገናም ሳኦል ሳይመጣ ከአንድ ቀን በፊት እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንዲህ ብሎ ገልጦለት ነበር። ነገ በዚህች ሰዓት ከብንያም አገር አንድ ሰው እሰድድልሃለሁ ልቅሶአቸው ወደ እኔ የደረሰ ሕዝቤን ተመልክቻለሁና ለሕዝቤ ለእስራኤል አለቃ ይሆን ዘንድ ትቀባዋለህ፥ ከፍልስጥኤማውያንም እጅ ሕዝቤን ያድናል።...

10:1 ሳሙኤልም የዘይቱን ብርሌ ወስዶ በራሱ ላይ አፈሰሰው፥ ሳመውም፥ እንዲህም አለው፦ በርስቱ ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶሃል የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ትገዛለህ፥ በዙሪያውም ካሉ ጠላቶቻቸው እጅ ታድናቸዋለህ።...

10:19-21 ዛሬ ግን ከመከራችሁና ከጭንቃችሁ ሁሉ ያዳናችሁን አምላካችሁን ንቃችሁ። እንዲህ አይሁን፥ ነገር ግን ንጉሥ አታንግሥልን አላችሁት። አሁንም በየነገዳችሁና በየወገናችሁ ወደ እግዚአብሔር ፊት ቅረቡ አላቸው። ሳሙኤልም የእስራኤልን ነገዶች ሁሉ አቀረበ፥ ዕጣውም በብንያም ነገድ ላይ ወደቀ። የብንያምንም ነገድ በየወገናቸው አቀረበ፥ ዕጣውም በማጥሪ ወገን ላይ ወደቀ። የማጥሪንም ወገን በየሰዉ አቀረበ፥ ዕጣውም በቂስ ልጅ በሳኦል ላይ ወደቀ ፈለጉትም፥ አላገኙትምም።

የእስራኤል ንጉሥን መፈለግ ለእ/ር ድንገተኛ ነገር ሳይሆን የሰውን እልከኛ ልብ የሚያውቅ እ/ር አስቀድሞ ሁሉን የሚያቅፍ ሃሳቡን በሙሴ ሰጥቷቸው ነበር:: ዘዳ 17:12-15

> ማናቸውም ሰው ቢኰራ፥ በዚያም አምላክህን እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚቆመውን ካህኑን ወይም ፈራጁን ለመስማት ባይወድድ፥ ያ ሰው ይሙት፥ ከእስራኤልም ዘንድ ክፋትን አስወግድ ሕዝቡም ሁሉ ሰምቶ ይፈራል፥ ከዚያም ወዲያ አይኰራም። አምላክህ እግዚአብሔር ወደሚሰጥህ ምድር በገባህ፥ በወረስሃትም ጊዜ፥ በተቀመጥህባትም ጊዜ። በዙሪያዬ እንዳሉት አሕዛብ ሁሉ በላዬ ንጉሥ አነግሣለሁ ስትል፥ አምላክህ እግዚአብሔር የመረጠውን በላይህ ታነግሣለህ ከወንድሞችህ መካከል የሆነውን በአንተ ላይ ንጉሥ ታነግሣለህ ወንድምህ ያልሆነውን ከሌላ ወገን ሰው በላይህ ንጉሥ ታደርግ ዘንድ አይገባህም።

**ይሂ ታሪክ ዛሬ የቤ/ክቲያንም ታሪክ ነው!**

ማቴ 19:8
እርሱም፦ ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።

እ/ር የማንንም ፈቃድ አይጫንም / አያስገድድም በአንጻሩ
ቅዱሳኑን በመንፈሱ ይመራል!

> ዮሐ 16:13
> 13 ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።
> ሮሜ 8:14
> 14 በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።

# ሙ·ሉ·/ፍጹ·ም ሰው ወደመሆን ማደግ ኤፌ 4:12-13

የነገሥታትን ልብ

ምሳ 21:1

የንጉሥ ልብ እንደ ውኃ ፈሳሾች በእግዚአብሔር እጅ ነው ወደ ወደደውም ያዘነብለዋል።

**እ/ርን እያወቁ ሊያውቁት ለማይወዱት**

**ሮሜ** 1:18-28

እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና። የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ። ...እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤

**እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መፈተን**

**ያዕቆብ** 1:13

13 ማንም ሲፈተን። በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም። 14 ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። 15 ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።16 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ አትሳቱ። 17 በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።

**1ቆሮ** 10:13

13 ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።

**1ዜና** 21:1

1፤ ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሣ፥ እስራኤልንም ይቈጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው።

3፤ ኢዮአብም። እግዚአብሔር ሕዝቡን በአሁኑ ላይ መቶ እጥፍ ይጨምር፤ ጌታዬ ንጉሥ ሆይ፥ ሁሉ የጌታዬ ባሪያዎች አይደሉምን? ይህን ነገር ጌታዬ ለምን ይሻል? በእስራኤል ላይ በደል ስለ ምን ያመጣል?

**በሁሉ ፈቃዱን መፈጸም የእ/ር ጥልቅ አሠራር ነው!**

**ዘፍ**50:20

ዮሴፍም አላቸው... እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው።

**ሮሜ** 8:28 እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን። (the working together of things...)

**ስለዚህ**

ኢሳ 55:9

ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤም ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው።

**ኤፌ** 2:1-3

በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።

**ኤፌ** 4:22-24

# ሙ·ሉ/ፍጹም ሰው ወደመሆን ማደግ ኤፌ 4:12-13

ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።

**ምሳ** 16:32
ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይሻላል፥ በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስዱ ይበልጣል።

**ምሳ** 2:11
ጥንቃቄ ይጠብቅሃል፥ ማስተዋልም ይጋርድሃል፥
**መክ** 10:8
ጉድጓድን የሚምስ ይወድቅበታል፥ ቅጥርንም የሚያፈርስን እባብ ትነድፈዋለች።